የሰ/መ/ቁ 235248

ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ሀይሉ ለማ -ጠበቃ ዓቅሩ ዳኘው -ቀረቡ

2ኛ. አቶ ደስታ ለማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ከውሉና ከቀረበው ማስረጃ አንጻር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ክርክሩ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ በሰሌዳ ቁጥር 03-60650 ኢት ለሆነ በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ተሽከርካሪ በመድህን ፖሊሲ ቁጥር MX/4MTCM/0068/13 የብር 1,300,000.00 (አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሺ) እንዲሁም በሰሌዳ ቁጥር 03-04466 ኢት በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ የጭነት ተጎታች በመድህን ፖሊሲ ቁጥር MX/4MTCM/0079/13 የብር 300,000.00 (ሶስት መቶ ሺ ) የአደጋ ጉዳት መድን ሽፋን ሰጥቻለሁ፡፡ እነዚህ ተሽከርካሪዎች ከጂቡቲ ወደ ዱከም ኢንዱስትሪ ዞን ዕቃ ጭነው በጉዞ ላይ እንዳሉ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ወለንጪቲ አከባቢ ተገልብጠው ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ አመልካች ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች ለማስጠገን በሂደት ላይ እያለ ተጠሪዎች ተሽከርካሪዎቹን ለማስጠገን ጥያቄ በማቅረባቸው አመልካች ዝርዝር መመሪያ በመስጠት የጥገና ፈቃድ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች በማስጠገን ለማስጠገኛ የወጣውን ወጪ አመልካች ክፍያ እንዲፈጽምላቸው

ጥያቄ አቅርበው በቀረበው ደረሰኝ መሰረት ብር 241,232.34 (ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር ከሰላሳ አራት

ሳንቲም) ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ነገር ግን አመልካች በቀረበውና ከፍሊሞን ተስፋየ ተሰጠ በተባለው ደረሰኝ ላይ ጥርጣሬ ስላደረበት ድርጅቱ ስለመመዝገቡና ስራ ላይ ያለ ስለመሆኑ እንዲጣራለት በደብዳቤ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ተጠቃሹ ድርጅት እ.ኤ.አ. 2019 በኃላ ግብይት ሲያደርግ ክፍያ የሚፈጸምበት ደረሰኝ በተቋሙ አለመመዝገቡ ገልጾ ከዚህ ንግድ ቤት በቀረበ ደረሰኝ መሰረት ለሚጠየቅ ክፍያ ጥያቄ ህጋዊነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ህጋዊ ደረሰኝ ተቆጥሮ ክፍያ እንዳይፈጸም የሚል ማረጋገጫ ተሰጥቶናል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች እና ተጠሪዎች በገባነው ውል አንቀጽ 5 ላይ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲከሰት የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ አመልካች በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ለካሳ የተከፈለው ክፍያ ተጠሪዎች ተመላሽ እንዲያደርጉ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም በማስጠንቀቂያው መሰረት ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም በመሆኑም ተጠሪዎች በህገወጥ መንገድ የወሰዱት የካሳ ክፍያ ሊመለስ ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ጉዳት ለደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ጥገና የሚውል መለዋወጫ አመልካች በሰጠው የዝርዝር መመሪያ መሰረት ፊሊሞን ተስፋዬ የከባድና ቀላል መኪና የማሽነሪ ዕቃዎች መለዋወጫ ከተባለ ድርጅት ተገዝቷል፡፡ ይኸው ድርጅት ህጋዊ የቫት ተመዝጋቢ ስለመሆኑ ህጋዊ የቫት ደረሰኝና የቫት ተመዝጋቢ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት፤ የተ.እ.ታ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤ የንግድ ስራ ፈቃድ ፤ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዳለው በማረጋገጥ የመለዋጫ ዕቃ ግዥ ተፈጽሟል፡፡ እንዚህም ማስረጃዎች የክፍያው ጥያቄ ለአመልካች ሲቀርብ ከክፍያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ አመልካችም አጠቃላይ የስራ አፈጻጸሙን በመገመገም ክፍያውን ለተጠሪዎች ፈጽሟል፡፡ ስለሆነም ተጠቃሹ ድርጅት እስከ 2020 ድረስ የቫት ተመዝጋቢ በመሆኑና ግብይቱም ህጋዊ በመሆኑ አመልካች የካሳ ክፍያ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍ/ቤት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን የቂርቆስ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር ቂ/ግ/5/24186/14 በቀን 06/08/2014 የተጻፈ ደብዳቤ እና የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ንግድ ጽ/ቤት ቁጥር ቂ/ክ/ከ/ወ4/ን/ል/ጽ/ቤት-447/2014 በቀን 05/08/2014 ዓ/ም የተጻፈ ከእነ አባሪው በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር

እንዲያያዝ አድርጎ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር

0056497915 በቀን 25/07/2010 ዓ/ም የተጨማሪ እሴቴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ በቀን 26/06/2010 ዓ/ም የንግድ ፈቃድ አውጥቶ በቀን 26/06/2010 ዓ/ም የደረሰኝ ህትመት የወሰደ መሆኑን የክፍለ ከተማው ገቢዎች ጽ/ቤት አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የወረዳው ንግድ ልማት ጽ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት በንግድ ዘርፍ ተመዝግቦ የቆየና የመለዋወጫ ችርቻሮ ንግድ ስራ እየሰራ እንደሚገኝ፤ እስከ 30/10/2012 ዓ/ም ድረስ የንግድ ፈቃድ የነበረው ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ በዚህ ማስረጃ መሰረት ክርክር የተነሳበት ጉዳይ በተከሰተ ጊዜ ድርጅቱ በህጋዊ መንገድ እየተንቀሳቀሰ እንደነበር ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን በመተላለፍ የተጭበረበረ ደረሰኝ ለአሁን አመልካች አቅርበዋል ሊባል ስለማይቻል በአሁን አመልካች የቀረበው ክስ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪዎች የካሳ ክፍያውን የመመለስ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታውን በይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ነገርግን የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ባቀረበው ማመልከቻ ክርክር የተነሳበት የመለዋወጫ ግዢ ተፈጽሟል፤ እንዲሁም ግዥ የተፈጸመበትን ደረሰኝ በማቅረብ አመልካች የካሳ ክፍያውን እንዲፈጽም ተጠሪዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የካሳ ክፍያው ተፈጽሟል፡፡ ነገር ግን አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት ደረሰኝ ህጋዊነት ላይ ጥርጣሬ ስላደረብን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የደረሰኙ ህጋዊነት እንዲጣራልን ጥያቄ ያቀረብን ሲሆን ጽ/ቤቱ በሰጠን ማስረጃ ተጠቃሹ ድርጅት እ.ኤ.አ. 2019 በኃላ ግብይት ሲያደርግ ክፍያ የሚፈጸምበት ደረሰኝ በተቋሙ አለመመዝገቡን ገልጾልናል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ንግድ ቤት በቀረበ ደረሰኝ መሰረት ለሚጠየቅ ክፍያ ጥያቄ ህጋዊነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ህጋዊ ደረሰኝ ተቆጥሮ ክፍያ እንዳይፈጸም የሚል አስተያየት ተሰጥቶናል፡፡ ግራ ቀኛችን በፈጸምነው የመድህን ውል አንቀት 5 ላይ መድህን የገባው ወገን ከመድህን ፖሊሲው ያልተገባ ጥቅም ለማግኝት ማናቸውም ህገወጥ ተግባር ፈጽሞ የውሉ ተጠቃሚ ለመሆን ከሞከረ ውሉ የሚሰጠውን ጥቅም እንደሚያጣ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪዎች ይህ የውል ድንጋጌ በሚቃረን መልኩ ህገወጥ ደረሰኝ በማቅረብ ያልተገባጥቅም አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በህገወጥ መንገድ

የወሰዱትን ካሳ እንዲመልሱ በማለት ያቀረብነውን አቤቱታ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ይታረምልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ከፍሲል በመግቢያችን የጠቀስነው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የስር ክርክራቸውን አጠናክረው አመልካች ጉዳት የደረሰባቸውን ተሸከርካሪዎች ለማስጠገን ባወጣው ጨረታ አሸናፊ ከሆነው ድርጅት የመኪና መለዋወጫ ግዥ ተገቢ የሆኑ ማስረጃዎች እንደ የተጨማሪ እንሴት ታክስ የምዝገባ ሰርተፍኬት፣ የንግድ ፈቃድ ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ምስክር ወረቀትና ህጋዊ ደረሰኝ ሁሉ ስለመኖሩ በማረጋገጥ የዕቃዎቹን ግዥ ፈጽመናል፡፡ ተጠሪዎች እነዚህ ማስረጃዎች ዕቃ ከተገዛበት ደረሰኝ ጋር በማያያዝ አመልካች ክፍያ እንዲፈጽምልን ጠይቀን የካሳ ክፍያው ተፈጽሟል፡፡ በመሆኑም የካሳ ክፍያው የተፈጸመው ህጋዊ ማስረጃ መሰረት አድርጎ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተመሳሳይ ክርክር አንስቶ ፍ/ቤቱ ባደረገው ማጣራት የቀረበውን ሰነድ ህገወጥነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የደረነኙ ህጋዊነት አስመልክቶ እ.ኤ.አ. 2019 በኃላ ግብይት ሲያደርግ ክፍያ የሚፈጸምበት ደረሰኝ በተቋሙ አለመመዝገቡ እንዲሁም ከዚህ ንግድ ቤት በቀረበ ደረሰኝ መሰረት ለሚጠየቅ ክፍያ ጥያቄ ህጋዊነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ህጋዊ ደረሰኝ ተቆጥሮ ክፍያ እንዳይፈጸም በማለት የሰጠውን አስተያየት በተመለከተ ጽ/ቤቱ እንዲህ ዓይነቱ ችግር ካለ አጣርቶ እርምጃ ከመውሰድ ውጪ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ውጤት አይኖረውም፡፡ ክርክር የተነሳበት ደረሰኝ ህገወጥ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት የመድህን ውል አንቀጽ 5 በመጥቀስ የካሳ ክፍያ ይመለስልን በማለት ያቀረበው አቤቱታ በህጉ አግባብ አይደለም፡፡ ድርጅቱ በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የሚፈልግበት ግዴታ ተወጥቷል አልተወጣም የሚለውን ማረጋገጥ የተጠሪዎች ስልጣን አይደለም፤ የምናጣረበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ተገቢውን ማጣራት እና ጥንቃቄ በማድረግ ግዥውን የፈጸምን በመሆኑ፣ የስር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔው የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ውሳኔውን በማጽናት እንዲያሰናብተን በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

በበኩላችን እንደመረመርነው የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠበት ጉዳት በተሸከርካሪዎቹ ላይ መድረሱ፤ ለጉዳቱ የኢንሹራንስ ሽፋን በአመልካች የተሰጠ መሆኑ፤ በጋራ በተደረገ ማጣራት ጉዳቱ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች የተካካዱበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነው ክፍያ ተፈፀመበት ደረሰኝ ህጋዊነት እና በዚሁ መነሻ የኢንሹራንስ ውሉ አንቀጽ 5 መጣስ ያለመጣሱ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ክርክሩንና ማስረጃዎችን መርምሮ ደረሰኝ ሰጥቶ ሽያጩን ያከናወነው የንግድ ድርጅት ክርክር የተነሳበት ጉዳይ በተከሰተ ጊዜ በህጋዊ መንገድ እየተንቀሳቀሰ እንደነበርና ግብይቱም በዚህ ጊዜ መፈጸሙን በማስረጃ በማረጋገጥ የአሁን ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን በመተላፍ የተጭበረበረ ደረሰኝ ለአመልካች አቅርበዋል ሊባል እንደማይችል፤ የውል ጥሰትም እንደሌለ አጣርቶ ወስኗል፡፡ ይኸው የፍሬ ነገርና የማስረጃ መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

እንደሚታወቀው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስልጣኑ ውጭ ነው፡፡ ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በመጨረሻ ከደረሱበት መደምደሚያ በመውጣት ሰበር ችሎቱ የሚደርስበት መደምደሚያ የሚነቀፍ ነው፡፡ ተቀባይነትም አይኖረውም፡፡

ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ክርክርና ማስረጃውን ለመመርመር ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን መዝነው ከፍሲል እንደተገለፀው ግብይቱ ህገወጥ ሊባል እንደማይችል፤ ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን በመተላፍ የተጭበረበረ ደረሰኝ አለማቅረባቸውን፤ የኢንሹራንስ ውሉም እንዳልተጣሰ ወስነዋል፡፡ ይኸው በማስረጃ የተረጋገጠ የፍሬ ነገር መደምደሚያና ውሳኔ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በድጋሚ ታይቶ የማስረጃ ምዘና ምክንያት ተሰጥቶ የሚለወጥበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም አጣሪ ችሎቱ በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ከውሉና ከቀረበው ማስረጃ አንጻር አጣርቶ ለመወሰን የሚል የፍሬነገር ጭብጥ በመያዝ ለሰበር ችሎት ማስረቀረቡ ሰበር ችሎቱ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ከፍሲል የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 89134 በቀን 26/08/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 293356 በቀን 19/12/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም